DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## SY23-24 ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC): የመግቢያ (Admission) ሂደት - የደረጃ መጠን (Rubric)

ለክፍል ደረጃዎች፡ 9 እና 10

**ስለ ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)፣ የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC) ውስጥ፣ ተነሳሽነትን የሚያሳዩ፣ ምሁራዊ የመሆን ፍላጎት፣ እና በቀለም ትምህርት ላይ የሚገጥሙ ፈታኝ በሆኑ ነገሮች የሚነሳሱ፣ እና በለጋ ዕድሜያቸው ወደ ኮሌጅ የኮርስ ስራዎች ዘለው የሚገቡ ጉጉት ያደረባቸውን፤ ምሁሮችን እንፈልጋለን።

**ስለ ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ ( Bard High School Early College DC)፣ የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ (Bard High School Early College) ውስጥ፣ የመግቢያ (admissions) ሂደታችን የሚያካትተው፣ ጽሁፍ (essay)፣ የርቀት (virtual) ቃለ-መጠይቅ፣ እና ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)ን - በ'My School DC' ማመልከቻ አማካኝነት ማስገባትን ነው። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልከቾች አንድ ዓይነት በሆነ የደረጃ መጠን (rubric) ይመዘናሉ። ምንም፣ አንድ-ብቻ የሆነ የመግቢያ (Admissions) ክፍል፤ ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም አመልካቾች፣ ለመግባት (admission) ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቅን እና ጽሁፍ (essay)ን ማጠናቀቅ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል። አመልካቾች፤ ለመግባት (admission) ብቁ ሆነው ከግምት-ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ፣ አነስተኛ መጠን (minimum) ጠቅላላ የውጤት ደረጃ የሆነውን ከ14 ነጥቦች ውስጥ 8፣ ማግኘት አለባቸው። 8 ነጥቦችን እና ከዚያ በላይ ያገኙ ሁሉም አመልካቾች፣ ለመግባት (admission) ብቁ የሚሆኑ እና በነጥቦቻቸው በአጠቃላይ ውጤት-ነጥቦች ደረጃ ቅደም-ተከተል መሠረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች፡** |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| ቃለ-መጠይቅ ~36% (5/14 ነጥቦች) | | **የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ** (Bard High School Early College DC)፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ የለውጥ ወኪል ለመሆን የጋለ ስሜት ያላቸው እና ለመማር ፍቅር ያላቸውን ተማሪዎችን ለመለየት ጥልቅ የሆነ እምነት አለው። ራሱን የሚገልጽ እና አዲስ ነገሮችን ለመማር ደስተኝነትን የሚያንፀባርቅ ተማሪን ማግኘት እንፈልጋለን።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY23-24 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (In Person) ወይም virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል። |
| ጽሁፍ (Essay): በ‘My School DC’ ማመልከቻ ውስጥ | ~36% (5/14 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ ጽሁፉም (essay) የተማሪውን በፕሮግራማችን ላይ ያለውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰቡ ያለውን ቁርጠኝነት፣ እና ተማሪዎች በጥልቀት-ማሰብና መገንዘብን (critical thinking) ችሎታቸውን - እንዴት እንደሚያሳዩ፣ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay) በ‘My School DC’ ማመልከቻው ውስጥ የሚጠናቀቅ፣ ወይም በአካል ተገኝቶ (in-person) ወይም በርቀት (virtual) - በብራድ (Bard) ውስጥ በሚደረግ ለሁሉም-ክፍት የሆነ (open house) ዝግጅት ላይ፤ ተሞልቶ-የሚጠናቀቅ ይሆናል።<br><br>ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ ለጽሁፍ (essay) የደረጃ መጠኑ (rubric)፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ ያተኮረ አይሆንም። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | ~29% (4/14 ነጥቦች) | **የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)**፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ጽሁፎቻቸውን (essay) እና ቃለ-መጠይቅ ይዘትን ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| | | የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ ኮሌጅ (Bard High School Early College)፣ ሁለት (2) የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)ን ይፈልጋል። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫ (recommendations)ን ካላስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ~15% መጠን (weight) የሚጠጋ ( 2 ነጥቦች)ን ወደ ቃለ-መጠይቁ እና ጽሁፉ (essay) ይጨምራል።<br><br>በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)፣ የድጋፍ ሰጪው፣ የተማሪውን በእጅጉ የተሟላ ምስል በተቻለ መጠን እንዳላቸው ለማረጋገጥ፤ በራሳቸው በኩል - ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን፣ ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታል። |